# የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

## የኢትዮጵያ የውጭ አገር የስራ ሥምሪት አፈፃጸም መመሪያ

**□. 90/2013**

ታኅሳስ 2012

አዲስአበባ

# ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

# የኢትዮጵያ የውጭ አገር ሥራ ስምሪት ተሻሽሎ የወጣ

# የአፈጻጸም መመሪያ፤

የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በኢትዮጵያ የውጭ አገር ሥራ ስምሪት አዋጅ ቁጥር 923/2008 አንቀጽ 75(2) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ሰኔ 2009 ዓ.ም ወጥቶ ስራ ላይ የነበረውን የሚተካ የተሻሻለ የአፈፃፀም መመሪያ አውጥቷል፡፡

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "የኢትዮጵያ የውጭ አገር ሥራ ስምሪት ተሻሽሎ የወጣ የአፈጻጸም መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡፡

1/ "አዋጅ" ማለት የኢትዮጵያ የውጭ አገር ሥራ ስምሪት አዋጅ ቁጥር 923/2008 ነው፡፡

2/ "የቤት ሠራተኛ" ማለት ከአሠሪ ጋር የቅጥር ግንኙነት በመፍጠር በመኖሪያ ቤት ውስጥ ያለውን ማንኛውም ስራ የሚሠራ ሰው ነው፡፡

3/ "የማሰልጠኛ ተቋም" ማለት ለውጭ አገር ሥራ ስምሪት የተመረጡትን የሙያ ዓይነቶች ዜጎችን ተቀብሎ የሚያሰለጥን የመንግስት ወይም አግባብ ካለው ባለስልጣን ህጋዊ ዕውቅና ያለው የግል የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋም ነው፡፡

4/ "ተመላሽ" ማለት በውጭ አገር በስራ ላይ ተሰማርተው ስራ ሲሰሩ ቆይተው ወደ አገር ቤት የተመለሱ ዜጎች ማለት ነው፡፡

5/ "8ኛ ክፍል ያጠናቀቀ" ማለት የ8ኛ ክፍልን ፈተና ወስደው ማለፊያ ውጤት በማግኘት ወደ 9ኛ ክፍል የተዛወረ ሰው ነው፡፡

6. "አግባብ ያለው ባለስልጣን" ማለት በከተማ አስተዳደር ወይም በክልል የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ህጎችን የማስፈጸም ሃላፊነት የተሠጠው አካል ነው፡፡፡

7. "ዝቅተኛ ደሞዝ" ማለት ኢትዮጵያ ከተቀባይ አገራት ጋር በምታደርገው የሁለትዮሽ የሥራ ስምሪት ስምምነት ወይም በስራ ውል የሚወሰን ዝቅተኛ የደመወዝ ወለል ማለት ነው፡፡

8. "የሥራ ውል"ማለት ከተቀባይ አገራት ጋር በሚደረገው የሁለትዮሽ የሥራ ስምምነት መሰረት ለስራ ወደ ውጭ አገር ለሚሄዱ ዜጎች መብት፤ ደህንነትና ጥቅም ለማስጠበቅ በአሰሪና ሰራተኛ መካካል የሚፈረም የስምምነት ሰነድ ነው፡፡

9. በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ በአዋጁ ትርጉም የተሰጣቸው ቃላትና ሃረጎች ለዚህ መመሪያም ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡
10. በወንድ ጾታ የተገለጸው ማንኛውም አገላለጽ ሴትንም ይጨምራል፡፡

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ፡-

1) መመሪያውን በሚያስፈጽም መንግስታዊ አካል፣ በውጭ አገር የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ፣ በኤጀንሲ አማካይነት ወይም በቀጥታ በሚደረግ ቅጥር የኢትዮጵያውያን የውጭ አገር ሥራ ስምሪት ግንኙነት ላይ፣
2) ለትርፍ በሚካሄድ ሥራ ላይ ላልተመሠረተ በቤት ሠራተኛነት ለመቀጠር ወደ ውጭ አገር በሚሄድ ኢትዮጵያዊ ላይ ፤ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

4. <u>ስለ ዝቅተኛ ደመወዝ</u>

በውጭ አገር ለሥራ የሚሠማሩ ዜጎች ዝቅተኛ የደመወዝ መጠን ከሙያ ሙያ፣ ከአገር አገር እና ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊለያይ የሚችል ቢሆንም ኢትዮጵያ ከተቀባይ አገር ጋር በምታደርገው የሁለትዮሽ የሥራ ስምሪት ስምምነት ወይም በሥራ ውል የሚወሰን ይሆናል፡፡

5. <u>ስለ ሥራ ውል</u>

ከተቀባይ አገራት ጋር በሚደረገው የሁለትዮሽ የሥራ ስምምነት መሰረት እንደሙያው ዓይነት ሊለያይ የሚችልና እንደአስፈላጊነቱ የሚሻሻል ሆኖ፣ ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ ሆኖ የቀረበው ሞዴል የሥራ ውል መነሻ የሥራ ውል ሆኖ ያገለግላል፡፡

6. <u>በውጭ አገር የግል ስራና ስራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ስላለባቸው ሰነዶች</u>

1. ማንኛውም አመልካች ፈቃድ ለማግኘት በአዋጁ አንቀጽ 24 ከተዘረዘሩት ሰነዶች በተጨማሪ በተቀባይ አገር የሚሰይመው ወኪል በሥራና ሠራተኛ አገናኝነት ተግባር ለመሰማራት የሚያስችለው መልካም ስነ ምግባር ያለው ስለመሆኑ አግባብ ካለው አካል የተሰጠው (Certificate of good conduct) እና ይሄው በተቀባይ አገር በሚገኘው ሚሲዮን እና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

2. በአዋጁ አንቀጽ 24(9) ሀ የተገለጸው እንደ ተጠበቀ ሆኖ በስራው ለመሳተፍ የሚያስችለው የወኪል ፈቃድ የታደሰ መሆን ይኖርበታል፡፡

7. <u>የማሳወቅ ግዴታ</u>

ማንኛውም ኤጀንሲ፡-

1) ለሥራ ወደ ውጭ አገር የላከው ሠራተኛ ከባድ የአካል ጉዳት ወይም የሞት አደጋ ሲደርስበት፣ እንዲሁም ወደ አገር ሲመለስ፣ ሲጠፋ፣ ሲታሰር፣አሠሪ ሲቀይር ወይም የመሳሰሉት ሁኔታዎች መከሰታቸውን እንዳወቀ ወዲያውኑ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱና እና አግባብ ላለው ባለስልጣን ማሳወቅ አለበት፡፡
2) በተዘጋጀው የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ መሰረት ለሥራ ወደ ውጭ አገር ስለላካቸው ሠራተኞች አጠቃላይ ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ ወር በገባ ባሉት 10 ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እና አግባብ ላለው ባለስልጣን ማቅረብ አለበት፡፡
3) ለሥራ ወደ ውጭ አገር ከላካቸው ዜጎች ያገኘው የውጭ ምንዛሪ በአገር ውስጥ ባንክ ገቢ የተደረገበትን ማስረጃ በየሩብ ዓመቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ከተጠቀሰው ሪፖርት ጋር በማያያዝ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
4) በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1, 2 እና 3) የተመለከቱትን ግዴታዎች ያልተወጣ በአዋጁ አንቀጽ 42(1)መሰረት እርምጃ የሚወሠድበት ይሆናል፡፡

8. <u>ስለ ፈቃድ ዕድሳት</u>

ማንኛውም ኤጀንሲ በሚኒስቴሩ የተሰጠውን ፈቃድ ለማሳደስ በአዋጁ አንቀጽ 33 ንዑስ አንቀጽ 2 ከተዘረዘሩት በተጨማሪ የሚከተሉትን ሰነዶች አሟልቶ ማቅረብ አለበት፡፡

1) በክልል ቅርንጫፍ ቢሮ ከፍቶ እየሰራ ከሆነ ከሚሠራበት ክልል አግባብ ካለው ባለሥልጣን የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ፣
2) የአደረጃጀት መዋቅር፤በወቅቱ በሥራ ላይ ያሉ ሠራተኞች እና የሥራ መደባቸውን የሚያሳይ ቻርት ከነፎቶግራፋቸው፣
3) የኤጀንሲው የሥራ ቦታ አድራሻና የቢሮው ይዞታ የራስ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ወይም ኪራይ ከሆነ የታደሰ የኪራይ ውል በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት የተረጋገጠ ዋና ቅጂ፣

4) በተቀባይ አገር ያለ ወኪል ሥራ ፈቃድ አገልግሎቱ ካበቃበት ጀምሮ በሁለት ወር ግዜ ውስጥ እንዲያሳድስ አድርጎ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

9. ፈቃድ ስለመተካት

1) ማንኛውም ኤጀንሲ የተሰጠው ፈቃድ ሲበላሽበት ምትክ ፈቃድ እንዲሰጠው ምክንያቱን በጽሑፍ በማስፈርና በመፈረም መጠየቅ አለበት፣

2) ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ጥያቄ ሲቀርብለት የተበላሸውን ፈቃድ እንዲመልስ እና አስፈላጊውን የፈቃድ አገልግሎት ክፍያ እንዲፈጽም በማድረግ በ2 የሥራ ቀናት ወስጥ ምትክ ፈቃድ ይሰጠዋል፣

3) ማንኛውም ኤጀንሲ የተሰጠው ፈቃድ የጠፋበት መሆኑን በጽሁፍ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እና አግባብ ላለው ባለሥልጣን ፈቃዱ በጠፋበት በሦስት የሥራ ቀናት ውስጥ በማሳወቅ ምትክ ፈቃድ እንዲሰጠው የሚከተሉትን ማስረጃዎች፤፡

ሀ) ፈቃዱ የጠፋበትን ምክንያት በዝርዝር የሚገልጽ የተፈረመበት የጽሁፍ መግለጫ፣

ለ) ፈቃዱ የጠፋበት ስለመሆኑ ከፖሊስ የተሰጠ የጽሁፍ ማስረጃ፣

ሐ) ፈቃዱ የጠፋበት ስለመሆኑ ለሕዝብ ይፋ ለማድረግ መጥፋቱን ለሚመለከተው አካል ካሳወቀበት ማግስት ጀምሮ ሰፊ ሽፋን ባለው ጋዜጣ፤ ወይም ሬዲዮ ና ቴሌቪዥን ያስነገረበት ማስረጃ፣ አሟልቶ ማቅረብ አለበት::

4) ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተመለከቱት ማስረጃዎች ተሟልተው መቅረባቸውን ሲያረጋግጥ፣ ኤጀንሲው አስፈላጊውን የፈቃድ አገልግሎት ክፍያ እንዲፈጽም በማድረግ ጥያቄው በቀረበ በ2 የሥራ ቀናት ወስጥ ምትክ ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

10. በአገር ውስጥ ተጨማሪ ቢሮ ስለመክፈት እና ስለማሳወቅ

1. ማንኛውም ኤጀንሲ በአገር ውስጥ ተጨማሪ ቢሮ መክፈት ሲፈልግ ቢሮውን ለመክፈት የፈለገበትን ክልል/ከተማ አስተደደር በመግለጽ ይሄው እንዲፈቀድ አግባብ ላለው ባለሥልጣን ጥያቄ ማቅረብ አለበት፣

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ተጨማሪ ቢሮ ለመክፈት ጥያቄ ያቀረበው ኤጀንሲ ለሥራ ወደ ውጭ አገር የላካቸውን ዜጎች መብትና ደህንነት በማስጠበቅ ረገድ ያለውን የአፈጻጸም ሁኔታ በመገምገም እና የማስፈጸም ብቃቱን በማረጋገጥ አግባብ ያለው ባለስልጣን ሊፈቅድ ይችላል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት አግባብ ያለው ባለሥልጣን ኤጀንሲው በአገር ውስጥ ተጨማሪ ቢሮ እንዲከፍት ሲፈቅድ ይህንኑ ለሚኒስቴሩ በአንድ ሳምንት ውስጥ በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ኤጀንሲው የተፈቀደለትን ቅርንጫፍ ቢሮ በ 15 የሥራ ቀናት ውስጥ ሰፊ ሽፋን ባለው ጋዜጣ ወይም ተደራሽነት ባለው ሬድዮና ቴሌቪዥን ለሕዝብ ይፋ በማድረግ ይህንኑ የሚያረጋገጥ ማስረጃ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱና ወይም አግባብ ላለው ባለሥልጣን ማቅረብ አለበት፡

11. <u>ስለ ማስረጃ አቀራረብ</u>

ከተቀባይ አገር ጋር በሚደረገው የሁለትዮሽ የስራ ስምምነት መሰረት ማንኛውም ኤጀንሲ ከውጭ አገር ሥራ ስምሪት ጋር በተያያዘ ከውጭ አገር የሚያቀርበው ማስረጃ በኢፌዲሪ ሚሲዮን እና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ መሆን ይኖርበታል፡፡

12. <u>ስለ ሰራተኛ ምዝገባና ምልመላ ስነ ስርዓት፤</u>

1) ማንኛውም ኤጀንሲ ሰራተኛን መመዝገብና መመልመል የሚችለው ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አቅርቦ ባጸደቀው የስራ መዘርዝር በማስታወቂያ ይፋ ካደረገ በኂላ መሆን አለበት፡፡

2) ማንኛውም ኤጀንሲ የግልጸኝነትና የተጠያቂነት አሰራር በመከተል የሚያካሂደውን የሠራተኛ ምዝገባና ምልመላ ሥነ-ሥርዓት የሚከተሉትን በዋነኝነት መያዝ ይኖርበታል፡-

ሀ) ስለ ሥራ ማስታወቂያ አወጣጥ፣

ለ) የሠራተኛው ዕድሜ፣

ሐ) የአመልካቾች አመዘጋገብ ምልመላና መረጣ ሂደት፤

መ) ለተመልማዩ ሰራተኛ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ከሚቀጠርበት ሥራ ጋር ብቻ ተዛማጅነት ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ፣

ሠ) በሠራተኛ ምልመላና መረጣ ወቅት በጾታ፣ በዘር፣ በኃይማኖትና በመሳሰሉት ምንም ዓይነት አድሎ እንዳይፈጸም ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ፣

ረ) ማንኛውም ኤጀንሲ በምዝገባና በምልመላ ጊዜ ያገኘውን የሠራተኛ መረጃ በሚስጢር መያዝ አለበት፡፡

ሰ) ማንኛዉም ኤጀንሲ ከምዝገባና ምልመላ በፊት የትኛዉንም ማስረጃ ከሰራተኞች ተቀብሎ መያዝ የለበትም፡፡

3) ማንኛውም ኤጀንሲ የሠራተኛ ምዝገባና ምልመላ ማካሄድ የሚችለው በተፈቀደለት ክልል/ከተማ መስተዳድር በከፈተው ቢሮ ውስጥ ብቻ ይሆናል፡፡

4) ማንኛውም ኤጀንሲ የሠራተኛ ምዝገባና ምልመላ ሲያካሂድ ተመዝጋቢዎች የነዋሪነት መታወቅያ ካርድ መያዛቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

13. <u>ጊዜያዊ የምልመላ ቦታ ስለሚፈቀድበት ሁኔታ</u>

1) በአዋጁ አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ኤጀንሲ እንደአግባቡ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ወይም አግባብ ላለው ባለሥልጣን የሚቀርበው ጊዜያዊ የሠራተኛ ምልመላ ቦታ ፈቃድ ጥያቄ ከሌሎች በተጨማሪ የሚከተሉትን በዋነኝነት ማካተት ይኖርበታል፡-

   ሀ/ የተገኙ ክፍት የሥራ መደቦች ዓይነትና ብዛት፣

   ለ/ የሥራ መደቦች የሚጠይቁት ሙያና ተፈላጊ ችሎታ፣

   ሐ/ የሚመለመሉ ሠራተኞች ብዛት፣

   መ/ ምልመላው የሚካሄድበት ቦታ፣

   ሠ/ ምልመላው የሚከናወንበት ቀን፣

   ረ/ ምልመላው የሚወስደው ጊዜ፣

2) ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የቀረበለትን ጥያቄ በመመርመር እና አስፈላጊነቱን በማረጋገጥ በ2 የሥራ ቀናት ውስጥ ሊፈቅድለት ይችላል፡፡

14. <u>የምልመላ አፈጻጸም ሪፖርት ስለማቅረብ</u>

ማንኛውም ኤጀንሲ በከፈተው ቢሮ ወይም በተፈቀደለት ጊዜያዊ የምልመላ ቦታ ያካሄደውን የምልመላ አፈጻጸም ሪፖርት ሚኒስቴሩ ባዘጋጀው ፎርማት መሠረት ምልመላው በተጠናቀቀ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ እንደ አግባቡ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ወይም አግባብ ላለው ባለሥልጣን ማቅረብ አለበት፡፡

15. <u>ስለ ስልጠና</u>

አግባብ ያለው ባለስልጣን፡-

1. በአዋጁ መሰረት መስፈርቱን የሚያሟሉ በውጭ አገር ሄደው መስራት የሚፈልጉ ዜጎችን እንደ የሥራ ፍላጎታቸው ዓይነት መዝግቦ ተገቢውን መረጃ ይይዛል፡፡
2. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የተመዘገቡትን እንደየስራ ፍላጎታቸው ወደ ሥልጠና እንዲገቡ ሁኔታዎችን ያመቻቻል ፡፡
3. በዚሁ አንቀጽ ንዑሥ አንቀጽ 2 መሰረት ስልጠና ወስደው የጨረሱትን የብቃት ምዘና እንዲወስዱ ያመቻቻል፡፡

4. ከመንግስትና ህጋዊ ዕውቅና ካለው የግል ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋም ስልጠና ወስደዉ የሙያ ብቃት ምዘና ያለፉት ዜጎች ማስረጃ ትክክለኛነት ከምዘና ማዕከላትና ከሚመለከተዉ የትምህርት ተቋም እንዲረጋገጥ ያደርጋል፡፡

16. <u>ወደ ውጭ አገር ለሥራ ተልከው የሚመለሱ ዜጎች የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ስለማመቻቸት፡-</u>

በአዋጁ አንቀፅ 64(4) መሰረት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ወደ ውጭ አገር ለሥራ ሄደው የሚመለሱ ዜጎችን እንዲቋቋሙ ፣ የመደገፍና የመከታተል ሥራዎችን ያከናውናል፡፡

1. **ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ፡-**
   ሀ. ወደ ውጭ አገር ለስራ ተልከው የተመለሱ ዜጎችን መረጃ በመያዝ እና በመተንተን አግባብነት ላለው ባለስልጣን እና ለሚመለከታቸው አካላት እንዲሰራጭ ያደርጋል፡፡
   ለ. ተመላሽ ዜጎችን ለመደገፍ ከሚመለከታቸው ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በመሆን የአቅም ግንባታ ስልጠና ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡
   ሐ. ተመላሾችን ዘላቂነት ባለውና አዋጭ በሆነ የሥራ መስክ እንዲሰማሩ እንደ አካባቢው የገበያ ፍላጎት ሁኔታ ጥናት በማድረግ አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡
2. **አግባብ ያለው ባለስልጣን፡-**

   ሀ. ተመላሽ ዜጎችን ለመደገፍ፤ ለማቋቋምና ለመከታተል የሚረዳ አደረጃጀትና በቂ የሠው ሃይል ማሟላት ይኖርበታል፡፡

   ለ. የክልሉን ተመላሾች መረጃ መሰረት በማድረግ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱና ከሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የሚደገፉበትና የሚቋቋሙበትን የፍላጎትና የገበያ ጥናት በማካሄድ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

   ሐ. የተመላሽ ዜጎችን መረጃ በማደራጀት፤ ድጋፍና በዘላቂነት የተቋቋሙትን መረጃዎች በማጠናከር ወቅታዊ ሪፖርት ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ያቀርባል፡፡
   መ. ተመላሾችን ለመደገፍና ለማቋቋም በሚሰሩ አገር በቀልና አለም አቀፍ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች ጋር በጋራ በመስራትና አፈጻጸሙን በመከታተል የዜጎችን ተጠቃሚነት ያረጋግጣል፡፡
   ሠ. ተመላሾች የህግ ምክር በሚያሥፈልጋቸው ጊዜ ድጋፍ ይሠጣል፡፡

## 17. የሥራ ውል ለማጽደቅ መሟላት ያለባቸው ሰነዶች

የሥራ ውል ለማፅደቅ የሚከተሉት ሰነዶች ተሟልተው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

1) ከተቀባይ አገራት ጋር በሚኖረው የሁለትዮሽ ስምምነት መሰረት በአሠሪው ተፈርሞ ስለትክክለኛነቱ በሚመለከተው የኢፌዲሪ ሚሲዮን እና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ እና እንደአግባቡ በአሠሪና በሠራተኛ፣ ወይም በአሠሪ፣ በሠራተኛ እና በኤጀንሲ የተፈረመ የሥራ ውል፣
2) የሥራ ስምሪት ቪዛ የተጻፈበት ቋንቋ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ውጭ ከሆነ የመተርጎም ህጋዊ ፈቃድ በተሰጠው አካል ወደ እንግሊዝኛ የተተረጎመ ከዋናው ቅጂ ጋር፣
3) ጊዜው ያላለፈ የሠራተኛው ፓስፖርት ፎቶ ኮፒ ከዋናው ቅጂ ጋር፣
4) ጊዜው ያላለፈ የሠራተኛው የቀበሌ መታወቂያ ኮፒ ከዋናው ቅጂ ጋር፤
5) የፓስፖርት መጠን ያላቸው የሠራተኛው ሁለት ጉርድ ፎቶግራፎች፣
6) ለሥራ በውጭ አገር የሚሰማራው ሠራተኛ የቅርብ ተጠሪ ጊዜው ያላለፈበት የቀበሌ መታወቂያ ኮፒ ከዋናው ቅጂ ጋር፣
7) ለሠራተኛው ከፖሊስ የተሰጠ የአሻራ ምርመራ ውጤት የሚያሳይ የምስክር ወረቀት፣
8) አገልግሎቱን ለመስጠት በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከተመረጠ ጤና ተቋም የተሰጠ የጤና ምርመራ ውጤት የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት፣
9) በውጭ አገር ለሥራ የሚሰማራው ሠራተኛ የቅድመ-ጉዞ ገለጻ የተከታተለ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ኮፒ ከዋናው ቅጂ ጋር፣
10) ቢያንስ የስምንተኛ ክፍል ትምህርት ማጠናቀቁን የሚያሳይ ማስረጃ፤
11) ወደ ውጭ አገር ለሥራ የሚሄድ ሠራተኛ በሚሰማራበት የሙያ መስክ ተመዝኖ ብቁ ስለመሆኑ የተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ኮፒ ከዋናው ቅጂ ጋር፣
12/ የሠራተኛው የግል ታሪክ የተሞላበት ቅጽ፣
13/ የሕይወትና የአካል ጉዳት የመድን ሽፋን ለሠራተኛው ስለመገባቱ የሚያሳይ ሰነድ፣
14/ ቀጣሪው መንግስታዊ ድርጅት ወይም ቀጥታ ቅጥር የተፈቀደለት የውጭ አገር አሠሪ ከሆነ በአዋጁ አንቀጽ 61 ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተው የዋስትና ፈንድ በባንክ ገቢ የተደረገበት ማስረጃ፣

## 18. የሥራ ውል ስለማጽደቅ

ሚኒስቴሩ በአዋጁ አንቀጽ 37 እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 18 የተመለከቱት ሰነዶች መሟላታቸውን እንዳረጋገጠ የቀረበውን የሥራ ውል በማጽደቅ ይመዘግባል፡፡

19. <u>የሥራ ውል ስለሚቋረጥበት ሁኔታ</u>

ከተዋዋይ ወገኖች አንዱ ወይም ሌላው በሥራ ውላቸው ውስጥ ለሥራ ውል መቋረጥ በምክንያትነት የተገለጸ ሁኔታ ሲፈጠር የስራ ውሉን የማቋረጥ መብት አለው፡፡

20. <u>የሥራ ውል ስለሚራዘምበትና ስለሚሻሻልበት ሁኔታ</u>

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 19 መሠረት ጸድቆ ስራ ላይ የዋለ የሥራ ውል ሲራዘም ፣ ሲቀየር ወይም ሲሻሻል ይሄው በተቀባይ አገር በሚገኘው ሚሲዮን እና በኢፌዲሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተረጋግጦ ሲቀርብ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ መፅደቅና መመዝገብ አለበት፡፡

21. <u>ስለ መድን ሽፋን</u>

በአዋጁ አንቀጽ 62 በተደነገገው መሠረት

1) ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ወደ ውጭ ሀገር ለስራ ለሚሰማሩ ዜጎች የተሻለ የመድን ሽፋን የሚሰጡትን የመድን ድርጅቶችን በጨረታ አወዳድሮ ይመርጣል፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በተመረጡ የመድን ድርጅቶች አሰሪው የዐረቦን ክፍያ በመፈጸሙ ለሰራተኛ የሕይወትና የአካል ጉዳት የመድን ሽፋን እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

3) አሰሪው ለሰራተኛው የሚገባው የመድን ሽፋን የጊዜ ገደብ በውጭ አገር ለስራ የሚሠማራ ሰራተኛ ከአሰሪ ጋር በተገባው የሥራ ውል የቆይታ ግዜ መሰረት ይሆናል፡፡፡

22. <u>አቤቱታ ስለመስማት</u>

1) ከሥራ ስምሪት ጋር በተያያዘ በኤጀንሲ ላይ የሚቀርብ ማንኛውም አቤቱታ የሚስተናገደው ሠራተኛው በተመለመለበት ክልል ብቻ ይሆናል፡፡

2) ከቀጥታ ቅጥር እና መንግስት ለመንግስት በሚደረግ ግንኙነት ከተፈጸመ ሥራ ስምሪት ጋር ተያያዞ የሚነሱ አቤቱታዎች ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ቀርበው የሚታዩ ይሆናሉ፣

3. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከአቤቱታ አፈታትና ከማስማማት ጋር በተያያዙ ጉዳዮች አግባብ ላለው ባለስልጣን አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣

23. <u>አንድ ወኪል ከስንት ኤጀንሲዎች ጋር መሥራት እንደሚችል ስለመወሰን</u>

1) በተቀባይ አገር ሥራና ሠራተኛ ለማገናኘት የሚያስችል ፈቃድ ያለው ሰው ወኪል ሆኖ መሥራት የሚችለው በኢትዮጵያ ውስጥ ሥራና ሠራተኛ ለማገናኘት የሚያስችል ፈቃድ ካላቸው ሁለት ኤጀንሲዎች ጋር ብቻ ይሆናል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በተቀባይ አገር ሥራና ሠራተኛ ለማገናኘት የሚያስችል ፈቃድ ያለው መንግሥታዊ አካል ከሆነ ወይም የግል ኤጀንሲዎች በኩባንያ ደረጃ ያቋቋሙት ከሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ ሥራና ሠራተኛ ለማገናኘት የሚያስችል የሥራ ፈቃድ ላላቸው እስከ አምስት ኤጀንሲዎች ወኪል መሆን ይችላል፡፡

3) በኢትዮጵያ ስራና ሰራተኛ ለማገናኘት የሚያሥችል ፈቃድ የተሰጠው ኤጀንሲ በተቀባይ አገር መሰየም የሚችለው አምስት ወኪሎችን ብቻ ነው፡፡፡

4) በተቀባይ አገር ያለ ማንኛውም ወኪል ከአንድ ኤጀንሲ የተቀበለውን ውክልና አቋርጦ ለሌላ ኤጀንሲ ወኪል መሆን የሚችለው ቀደም ሲል በወከለው ኤጀንሲ አማካይነት ለሥራ ወደ ውጭ አገር የተላኩ ዜጎች የስራ ውል ጊዜያቸው ከተጠናቀቀ በኋላ ብቻ ይሆናል፡፡

24. <u>ፈቃድ ስለመመለስ እና የዋስትና ገንዘብ ስለመልቀቅ</u>

1) ማንኛውም ኤጀንሲ በአዋጁ አንቀጽ 60 ንዑስ አንቀጽ 5 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የተሰጠውን ፈቃድ በመመለስ ለሥራ ወደ ውጭ አገር ለላካቸው ዜጎች መብትና ደህንነት ማስከበሪያ በዝግ ሂሳብ በባንክ ያስያዘው የዋስትና ገንዘብ እንዲለቀቅለት ጥያቄ ሲያቀርብ የሚከተሉትን አሟልቶ ማቅረብ አለበት፡፡

ሀ) የተሰጠውን ፈቃድ ለመመለስ ከፈቃዱ ጋር የቀረበ የጽሁፍ ማመልከቻ፣

ለ) በተዘጋጀው ቅጽ መሠረት ፈቃድ ካወጣበት ጊዜ ጀምሮ ለሥራ ወደ ውጭ አገር የላካቸው ዜጎች ያሉበትን ሁኔታ የሚያሳይ ዝርዝር ሪፖርት ማቅረብ፣

ሐ) ከግብር ነጻ መሆኑን የሚገልጽ ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የተሰጠው ክሊራንስ፣

መ) ለሥራ ወደ ውጭ አገር ከላካቸው ዜጎች መብት መጣስ ጋር በተያያዘ ነፃ መሆኑን የሚያረጋግጥ አግባብ ካለው የፍትህ አካል የተሰጠው ማስረጃ፣

ሠ) ቢሮ ከፍቶ ከሚሰራበት ክልል አግባብ ባለው ባለሥልጣን የተሰጠው ክሊራንስ፣

2) ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ፦ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተዘረዘሩት ሰነዶች ተሟልተው መቅረባቸውን በማረጋገጥ፣

ሀ) ለሥራ ወደ ውጭ አገር ከተላኩ ዜጎች ጋር በተያያዘ በኤጀንሲው ላይ የቀረበ ክስ ወይም አቤቱታ አለመኖሩን ከፍትህ አካላት፣በሠራተኛ ተቀባይ አገራት ከሚገኙ የኢትዮጵያ ሚስዮኖች እና ከሌሎች አግባብነት ካላቸው አካላት በማጣራት፣

ለ) ኤጀንሲው ለሥራ ወደ ውጭ አገር ከላካቸው ዜጎች መብት ጋር በተያያዘ የሚቀርብ የመብት ጥያቄ መኖር አለመኖሩን ለማረጋጥ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ለሁለት ወር

የሚቆይ ማስታወቂያ ለሕዝብ ይፋ በማድረግና በዚህ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የቀረበ የመብት ጥያቄ አለመኖሩን በማረጋጥ፣

ሐ/ ለስራ ተልከው የውል ጊዜያቸው ያልተጠናቀቁ ዜጎች አለመኖራቸውን ከዳታ ቤዝ በማጣራትና በማረጋገጥ፤

ኤጀንሲው ጥያቄ ባቀረበ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ በባንክ ያስያዘው ገንዘብ እንዲለቀቅለት ያደርጋል፡፡

3) በቀድሞ አዋጅ ቁጥር 632/2001 የስራ ፈቃድ አውጥተው በመንግስት የውጭ አገር ስራ ስምሪት አገልግሎት እንዲቆም በመደረጉ ምክንያት ሰራተኛ ሳይልኩ የቀሩ ኤጀንሲዎች ያሥያዙት የዋስትና ገንዘብ እንዲለቀቅላቸው ሲያመለክቱ ሰራተኛ ያለመላከቸው ከዳታ ቤዝ በማጣራትና በማረጋገጥ በቀጥታ ወደ ባንክ በመጻፍ በዝግ የተያዘ ገንዘብ እንዲለቀቅ ይደረጋል፡፡

4) በቀድሞ አዋጅ ቁጥር 632/2001 መሰረት የስራ ፈቃድ አውጥተው ዜጎችን ለስራ ወደ ውጭ አገር ሲልኩ የነበሩ ኤጀንሲዎች ከዘርፉ ለመውጣት በዝግ ሂሳብ ያስቀመጡ የዋስትና ገንዘብ እንዲለቀቅላቸው ሲያመለክቱ በዚሁ የአፈፃጸም መመሪያ አንቀጽ 24(1) እና (2)መሰረት የሚለቀቅ ይሆናል፡፡

5) ከዚህ በላይ በአንቀጽ 24(4) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በአዲሱ የውጭ አገር ስራ ስምሪት አዋጅ ቁጥር 923/2008 መሰረት ፈቃድ አውጥተው ስራ ላይ የተሰማሩ ኤጀንሲዎች በቀድሞ አዋጅ ቁጥር 632/2001 በዝግ ሂሳብ አስቀምጠው የነበረው የዋስትና ገንዘብ በቀጥታ የሚለቀቅላቸው ቀደም ሲል ከተላኩት ዜጎች የሚቀርበው የክፍያ ጥያቄ በአዲሱ አዋጅ በዝግ ሂሳብ ካስቀመጡት የዋስትና ገንዘብ ላይ እንዲከፈላቸው ስምምነታቸውን በጽሁፍ ሲገልጹ እንዲለቀቅላቸው ይደረጋል፡፡

## 25. የዋስትና ፈንድ ክፍያ አፈፃፀም፤

በአዋጁ አንቀፅ 61 መሰረት እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት በወጣው ደንብ ቁጥር 434/2011 መሰረት መንግስት ለመንግስትም ሆነ በቀጥታ ቅጥር አማካኝነት ለስራ ወደ ውጭ አገር ተሰማርቶ የነበረ ሠራተኛ በስራ ውል መጣስ ምክንያት ከዋስትና ፈንድ እንዲከፈል የሚቀርብ የክፍያ ጥያቄ የሚከተሉትን ሰነዶች ተሟልተው ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

ሀ/ ሠራተኛው ወይም ህጋዊ ወራሹ በስራ ውሉ መሰረት የደሞዝ ክፍያ ሳይፈፀምለት መቅረቱን በማመልከቻ በፅሁፍ ሲያቀርብ፣

ለ/ ሠራተኛ በህጋዊ መንገድ የስራ ውል ጸድቆለት መሄዱን ከዳታ ቤዝ መረጃ መኖሩ ሲረጋገጥ፣

ሐ/ የቀረበው የደሞዝ ክፍያ ጥያቄ ትክክለኛነቱ ሰራተኛው በነበረበት አገር ክፍያ ያልተፈጸመ መሆኑን በሌበር አታሼ ወይም ሚሲዮን እና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ ማስረጃ ሲቀርብ፣

መ/ ሰራተኛው ያቀረበው የደሞዝ ክፍያ ጥያቄ ህጋዊነት ተረጋግጦ የክፍያ ማዘዣ ሲቀርብ በፋይናንስ ደንብ መሰረት እንዲከፈል ይደረጋል፣

26. <u>ስለ ቁጥጥር</u>

በአዋጁ አንቀጽ 20(3ሀ) መሰረት ለኤጀንሲ የስራ ፈቃድ ከመስጠቱ፤ ከመታደሱና ነባሩን የቢሮ አድራሻ ከመለወጡ በፊት የተሟላ ቢሮ፤ የምልመላ ስርአትና የቅድመ ቅጥር ገለጻና የምክር አገልግሎት መስጫ ቦታና ባለሙያ ማሟላቱን ማረጋገጥን በተመለከተ፤

1. የስራ ቦታ አካባቢ፤የሠው ሃይልና የቢሮ ስፋት፤
   ሀ. ለተገልጋዮች በቀላሉ ተደራሽና ለአገልግሎት አሰጣጥ አመቺ፤ ግልጽና ከዋናው ወይም ከመጋቢ መንገድ ከ 100 ሜትር በላይ ያልራቀ መሆን አለበት።
   ለ. ስራ የሚያከናውኑ ቢያንስ ስራ አስኪያጅ፤ አይቲ ባለሙያ፤ምክር ሰጪ፤አቤቱታ አስተናጋጅ፤ ጉዳይ አስፈጻሚና ጸሃፊ የሰው ሃይል ሊኖሩት ይገባል።
   ሐ. የዋናው ቢሮ የክፍሉ ስፋት ቢያንስ 30 ካሬ ሜትር፤ የተገልጋዮች መቀመጫ ቢያንስ 6 ወንበሮች ያሉት፤ የምክር መስጫ ቢሮ ቢያንስ 16 ካሬ ሜትር ሆኖ ለተገልጋዮች መቀመጫ እስከ 12 አርምቼር ወንበሮች ያሉት በጠቅላላው የቢሮ ስፋቱ ከ46 ካሬ ሜትር ያላነሰ መሆን ይኖርበታል።

2. በአዋጁ አንቀጽ 24(7) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ከግል ድርጅቶች ለሚቀርቡ የስራ ልምድ ግብር ስለመከፈሉ ከገቢዎች ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል።
3. በክልል/ከተማ አስተዳደር የሚከፈቱ ቅርንጫፍ ቢሮዎች ለአገልግሎት አሰጣጥ አመቺነት ያላቸው ሆነው፤
   ሀ/ በክልል/ከተማ አስተዳደር ከ3 ያለነሰ የሰው ሃይል፤
   ለ/ በክልል/ከተማ አስተዳደር ከ30 ካሬ.ሜ የቢሮ ስፋት ያለነሰ፤
   ሐ/ በክልል/ከተማ አስተዳደር ከ10 ወንበሮች ያላነሱና የቢሮ መገልገያዎች፤ የመረጃና ዳታ ማጠናቀሪያ ኮምፒዩተር ሊኖረው ይገባል።

27. <u>የመተባበር ግዴታ፤</u>

ማንኛውም ሰው ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

28. <u>የተሻረ መመሪያ፣</u>

የኢትዮጵያ የውጭ አገር ስራ ስምሪት አዋጅ ቁጥር 923/2008 ለማስፈጸም ሰኔ 2009 የወጣ የአፈጻጸም መመሪያ በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

29. <u>መመሪያ ስለማሻሻል፤</u>

ይህ መመሪያ እንደ አስፈላጊነቱ ሊሻሻል ይችላል፡፡

30. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከ ታህሣሥ 17 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ኤርጎጌ ተስፋዬ(ፒኤችዲ)

የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚስቴር ሚንስትር

## ሞዴል የስራ ውል

ይህ የስራ ውል ከዚህ በታች በተመለከቱት ተዋዋይ ወገኖች ተፈጽሟል

ሀ.አሰሪ

ሙሉ ስም ____________________

አድራሻ ________________

ፖ.ሳ.ቁ________________

ስልክ ቁጥር____________________

ለ. ኤጀንሲ ________________

ሙሉ ስም ____________________

አድራሻ________________

ፖ.ሳ.ቁ________________

ስልክ ቁጥር____________________

ሐ.የኤጀንሲ/ወኪል/

ሙሉ ስም ____________________

አድራሻ________________

ፖ.ሳ.ቁ________________

ስልክ ቁጥር____________________

መ.ሰራተኛ________________

ሙሉ ስም ____________________

እድሜ________________

የጋብቻ ሁኔታ____________________

የትምህርት ደረጃ________________

ሙያ________________

የፓስፖርት ቁጥር ____________________

ፓስፖርት የተሰጠበት ቀንና ቦታ__________

_________

በአደጋ ጊዜ የቅርብ ተጠሪ

ሙሉ ስም ____________________

አድራሻ________________

ፖ.ሳ.ቁ________________

ስልክ ቁጥር____________________

በሚከተሉትግዴታዎችና ሁኔታዎች ለመገዛት ፈቅደዋ ተዋውለዋል

1. ተቀባይ ሀገር____________________
2. የስራው ስፍራ ____________________
3. የስራው ውል የሚቆይበት ጊዜ
   _____ሰራተኛው ለስራ ወደሚሰማራበት ስፍራ ለመሄድ ከኢትዮጵያ ከሚለቅበት ጊዜ አንስቶ
4. የሙያው አይነት ________________
5. የወር ደሞዝ ________________
6. ክፍያው የሚፈጸምበት ጊዜ ________
   _____
7. መደበኛ የስራ ሰአት________________
   _____
8. የእረፍት ሰአት ________________
9. የትርፍ ሰአት ስራ ክፍያ____________
   _____

ሀ.ከመደበኛው የስራ ሰአት በላይ ለሚሰራ ስራ

ለ.በተወሰነ የእረፍት እና የበአል ቀናት ለሚሰራ ስራ

10. እረፍት ከሙሉ ክፍያ ጋር
    ሀ.የሳምን እረፍት
    የአመት ፍቃድ
    የህመም ፍቃድ
    ሌሎች
11. ነጻ የደርሶ መልስ ትኬት
12. በቂ የተመጣጠነ ነጻ ምግብ እና ምቹ የመኖሪያ ቤት ወይም ማካካሻ አበል
13. ነጻ ህክምና አገልግሎት ከመድሀኒት አቅርቦት ጭምር
14. በአሰሪው የተገባ የሰራተኛው የግል ህይወት እና አደጋ ኢንሹራንስ
15. በዚህ የስራ ውል ቆይታ ጊዜ ውስጥ ሰራተኛው

## Model Work Contract

**This work contract shall be executed and concluded between and to:**

**A. Employer:**

**Full Name..................................**

**Title......................................**

**P.O. Box...................................**

**Phone No...................................**

**B. Agency:**

**Full Name..................................**

**Title......................................**

**P.O. Box...................................**

**Phone No. .................................**

**Fax........................................**

**C. Agency Representative**

**Full Name..................................**

**Title......................................**

**P.O. Box...................................**

**Phone No. .................................**

**Fax........................................**

**D.Employee:**

**Full Name..................................**

**Age........................................**

**Sex........................................**

**Social Status..............................**

**Educational Level..........................**

**Qualification..............................**

**Passport Number............................**

**Date and Place of Issued...................**

**The person contracted at the time of the accident:**

**Full Name..................................**

**Title......................................**

**P.O. Box...................................**

**Telephone number...........................**

**Voluntarily bound by the following terms and conditions**

**1. Host Country.............................**

**2. Employment Site..........................**

**3. Duration of contract.....................**

**Commencing of Employee's Departure from Ethiopia to the employment site**

**4. Profession Type..........................**

**5. Monthly Salary...........................**

**6. The biography of the payment...........**

**7. Normal working hours.....................**

**8. Rest time................................**

**9. Overtime:................................**

**A. To work more than normal.**

**B. To work on a specific day off and holiday.**

**10. Full Payment Leave:**

**Weekly Rest................................**

**Annual Vacation............................**

**Sick Leave.................................**

**Others.....................................**

**11. Free Round Trip Ticket.**

**12. Free, Adequate and Balanced Food, Free Housing Allowance or Compensation Allowance.**

**13. Free Medical Service and Facilities including Medicine.**

**14. Personal Life and Accident Insurance Covered by the Employer**

## عقدعملنموذجي.

يتم تنفيذ عقد العمل هذا وإبرامه بين الأطراف التالية:

أ. صاحب العمل:

الاسم الكامل..............................................

المهنة......................................................

صندوق البريد...............................................

رقم الهاتف...................................................

ب. مكتب التوظيف:

الاسم الكامل..............................................

المهنة......................................................

صندوق البريد...............................................

رقم الهاتف...................................................

فاكس..........................................................

ج. الموظف:

الاسم الكامل..............................................

العمر ........... الجنس ...........................

الحالة الاجتماعية..........................................

المستوى التعليمي...........................................

المؤهل......................................................

رقم جواز السفر.............................................

تاريخ ومكان الإصدار.......................................

الشخص القريب للاتصال به في حال وقوع حادث :

الاسم الكامل..............................................

العنوان......................................................

صندوق البريد...............................................

رقم الهاتف...................................................

يلتزمون طوعاً بالشروط والأحكام التالية:

1. البلد المضيف...........................................

2. موقع العمل.............................................

ቢሞት አስክሬኑ እና የግል ንብረቶቹ በአሰሪው ወጪ ወደ ኢትዮጵያ መመለስ።ምናልባት አስክሬኑ ወደ ኢትዮጵያ መላክ የማይችል ሆኖ ሲገኝ የሟችን የቅርብ ዘመድ እና ወይም የኢትዮጵያ ሚሲዮን (ኤምባሲ፣ቋሚ መልእክተኛ ጽ/ቤት ጉዳይ አስፈጻሚ ዌም የክብር ቆንስላ)በሚያደርጉት የቅድሚያ ስምምነት መሰረት ተገቢውን ማድረግ ይቻላል።

16. ሰራተኛው አግባብ ባለው የባንክ አሰራር ወይም ህጋዊ በሆነ በሌላ መንገድ በመጠቀም ደመዎዙን ወደ አገሩ መላክ እንዲችል አሰሪው መርዳት ይኖርበታል

17. የስራ ው መቋረጥ የስራ ውሉ የሚቋረጥበት ምክንያቶች የሚከተሉትን ሊጨምር ይችላል

ሀ.በአሰሪው የሚደረግ የስራ ውል መቋረጥ አሰሪው አንዳችም ማስጠንቀቂያ ለሰራተኛው ሳሰጥ ይህንን የስራ ውል በሚከተሉት በቂ ምክንያቶች ሊቋረጥ ይችላል።በሰራተኛው ጉልህ የስነምግባር ብልሹነት የአሰሪውን ህጋዊ ትእዛዝ ሆነ ብሎ ያለመወጣት ልምድ ያለበቂ ምክንያት በተደጋጋሚ ከስራ የመቅረት፣የድርጅቱን ሚስጢሮች የመግለጽ የመሳሰሉት ወይም ይህን የስራ ውል ሲጥስ

ለ. በሰራተኛውየሚደረግ የስራ ው መቋረጥ በአሰሪው አንዳችም ማስጠንቀቂ ለአሰሪው ሳይሰጥ ይህንን የስራ ውል በሚከተሉት ምክንቶች ሊያቋርጥ ይችላል።የአሰሪው ወይም የወኪሉ ከባድ ስድብ አሰሪው ወይም ወኪሉ ለሰራተኛው የሚያደርገው ኢሰብአዊነትና አግባብነት የሌለው አያያዝ የአሰሪውን ወይም የወኪሉን በሰራተኛው ላይ የወንጀል ድርጊት መፈጸም ወይም የወኪሎች ህጎችን የዚህን የስራ ውል መጣስ።

ሐ. ሰራተኛው የ30 ቀን የቅድሚ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ለአሰሪው በመስጠት ይህንን የስራ ውል በማናቸውም ምክንያት ማቋረጥ ይችላል

18. እድሳት ይህ የስራ ውል በጋራ ስምምነት ሊታደስ ይችላል

19. ማሻሻል እና መለወጥ በዚህ የስራ ውል ላይ ሊደረግ የሰራተኛውን ጥቅም በሚቀንስ ማሻሻያ ለውጥ እና የመሳሰሉት የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ፈቃድ ከሌለው በቀር ውጤት አይኖረውም።

20. የስራ ክርክር አፈታት ማንኛውም ከስራ ውሉ ጋር የተዛመደ የይገባኛል ጥያቄ እና ቅሬታ በኩባንያው ፖሊሲ ፣መመሪያ፣ደንብ እና ህጎች መሰረት ይፈታል ።ይህ ሳይሳካ በቀረ ጊዜ አግባብ ያለው የኢትዮጵያ ሚሲዮን (የኢትዮጵያ ኤምባሲ ቋሚ መልእክተኛ ጽ/ቤት ፣ጉዳይ አስፈጻሚ ወይም የክብር ቆንጽላ) ተሳታፊ በሆነበት ጉዳዩ በስምምነት እንዲፈታ ጥረት ይደረጋል ።ጥረቱ ካልተሳካም ጉዳዩ ቅሬታ ባለው ወገን ምርጫ በተቀባይ አገር ወይም በኢትዮጵያ ለሚገኘው ባለስልጣን ወይም አግባብ ለሆነ የመንግስ አካል እንዲቀርብ ያደርጋል።

21. ሰራተናው አሰሪውን ኩባንያ መመሪያ ማክበር እና አግባብ ባለው የተቀባዩ አገር ህጎች መገዛት ይኖርበታል።

22. አሰሪው ለሰራተኛው አስፈላጊውን የመግቢ ቪዛ እና ህጋዊ የስራ ፍቃድ ከተቀባዩ አገር የማግኘት ሀላፊነት አለበት ።

23. ተፈጻሚነት ያለው ህግ ከላይ ከተመለከቱት አንቀጾች ጋር የሚጣጣሙ ሌሎች ግዴታዎችና

**15. In the event of death of the employee during the term of this agreement his remains and personal belongings shall be repatriated to the point of origin. In case the repatriation of remains is not possible, the same may be disposed of as appropriate upon prior approval of the employee's next of kin and/or by the appropriate Ethiopian mission (Ethiopian Embassy permanent mission general consulate office charge de affairs or honorary consulate general).**

**16. The employer shall assist them in remitting his salary through the proper banking channel or other means authorized by law.**

**17. Termination: Grounds for termination of the employment contract may include the following.**

**a. Termination by the Employer: The employer may terminate this contract without serving any notice to the employee for any of the following just cases: serious misconduct, disobedience of employer's lawful orders, habitual neglect of duties, absenteeism, reveling secrets of establishment or when the employee violets terms of this Contract of agreement.**

**b. Termination by the Employee: The employee may terminate this contract without serving any notice to the employer for any of the following just causes; serious insult by the employer or his representative; inhuman and unbearable treatment accorded to the employee by the employer or his representative.**

**The employee may terminate this contract for any reason by serving 30 days advance written notice to the employed**

**18. Renewal: This contract may be renewed by mutual agreement.**

**19. Modification and alteration: Any modification,**
**Alternation and the like made in this contract unfavorable to the worker without the consent of the Ministry of Labor and Social Affairs shall not have any effect.**

**20. Settlement of Disputers: All claims and complaints related to the employment contract of the employee shall be settled in accordance with the companies' policies rules, regulations, and law . In case the settlement the matter shall be settled amicably with the involvement of the appropriate Ethiopian Mission (Embassy, permanent mission, General consulate office charge de affairs or honorary consulate General). In case the amicable settlement fails, the matter shall be submitted to the competent or appropriate government body in (host country) or in Ethiopia at the option of the complaining party.**

**3. مدة العقد**

..........................................................

(من تاريخمغادرةالموظفمنإثيوبياإلىالموقعالعمل)

**4. نوع المهنة**

..........................................................

**5. الراتب الشهري**

..........................................................

**6. تفاصيل المدفوعات**

..........................................................

**7. ساعات العمل العادية**

..........................................................

**8. ساعة الراحة**

..........................................................

**9. أجر العمل**

**الإضافي:..........................................................**

**ا. للعمل أكثر من ساعات العمل العادية.**

**ب. للعمل في يوم راحة محدد وعطلة.**

**10. إجازة مدفوعةبالكامل:**

الراحة الأسبوعية

..........................................................

إجازة

سنوية..........................................................

إجازة

مرضية..........................................................

غير

ذلك..........................................................

**11. تذكرة ذهاب وإياب مجانية.**

**12. طعاممجاني وكافي ومتوازن وسكن مجانيأو تعويض مالي.**

**13. خدماتومرافق طبية مجانيةبمافيذلكالدواء.**

**14. تأمينعلىالحياةالشخصيةوالحوادثيغطيهاصاحبالعمل.**

**.15**

**فيحالةوفاةالموظفخلالمدةهذهالاتفاقية،يتمإعادةرفاتهوممتلكاتهال شخصيةإلىوطنهالأصلي.**

**فيحالةعدمإمكانيةإعادةرفاتهإلىوطنه،يمكنالتصرفحسبالاقتضاءبن اءًعلىموافقةمسبقةمنأحد أفراد العائلةو / أوالبعثةالإثيوبيةالمناسبة (السفارةالإثيوبيةأو البعثة الدائمةأوالمسؤولعنمكتبالقنصليةالعامةأوالقنصليةالعامةالفخرية ).**

**16- يقومصاحبالعملبمساعدة الموظففيتحويلراتبهعنطريقالقناةالمصرفيةالمناسبةأوغيرهامنالو سائلالقانونية.**

**17. الإنهاء: قدتشملأسبابإنهاء عقد العملمايلي.**

**ا. إنهاءالعملمنجانبصاحبالعمل:**

**يجوزلصاحبالعملإنهاءهذاالعقددونتقديمأيإشعارإلىالموظفعنأيمنال حالاتالتالية فقط:**

**سوءالسلوكالجسيم،عدمتنفيذالأوامرالقانونيةلصاحبالعمل،الإهما لالدائمللواجبات،التغيبعنالعمل،إفشاءأسرارالمؤسسةأوعندماينته ك الموظفشروطهذاالاتفاق.**

**ب. الإنهاءمنقبلالموظف:**

**يجوزللموظفإنهاءهذاالعقددونتقديمأيإخطارإلىصاحبالعمللأيمنالأ سبابالتالية فقط؛إهانةخطيرةمنقبلصاحب العملأومنيمثله؛معاملةلاإنسانيةوغيرمحتملةللموظفمنقبلصاحبال عملأومنينوبعنه.**

የስራ ሁኔታዎች አግባብ ባላቸው ህጎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

24. አሰሪው ይህንን የስራ ውል ቢጥስ በጋራ እና በተናጠል ተጠያቂ ለመሆን ተስማምቷል።

25. ይህ የስራ ውል በአራት ቅጂ ተዘጋጅቶ ኤጀንሲው አሰሪው እና ሰራተኛው አንድ አንድ ይደርሳቸዋል።አንድ ኮፒ በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲቀመጥ ይደረጋል።

ይህ የስራ ውል ዛሬ
ቀን ተፈራርመናል።

ሰራተኛው :
አሰሪ

የግል ስራና ሰራተና አገናኝ ኤጀንሲ

ፊርማ

የአጀንት /ወኪል/

ፊርማ

እማኞች

1. ሙሉ ስም ____________________
አድራሻ____________________
ስ.ቁ ፊርማ ____
______________

2. ሙሉ ስም ____________________
አድራሻ____________________
ስ.ቁ__________________ፊርማ____
______________

**21. The employee shall observe employer's company rules and abide by the pertinent laws of the host country.**

**22. The employer is responsible to obtain the necessary entry visa and legal work permit for the employee form the host country.**

**23. Applicable law: Other terms and conditions of employment which are consistent with the above provisions shall be governed by the pertinent laws..........................**

**24. If this contract of employment is violated by the employer the agency has agreed to be held responsible jointly and severally.**

**25. This contract of employment is drawn in four the Agency , the employer and the employee will be provided one each and the one copy will be deposited in the Ministry of Labor and Social Affairs.**

**We here by sign this contract this: ------day-----**

**Private Employment agency**
**Employer Employee**

**Signature**

**Agency Representative**

**Signature**

**Witnesses:**
**1. FullName**
**Address----------------------------------------**
**Tel: No----------------- Signature-----------**
**2. Full Name-------------------------------------**
**Address----------------------------------------**
**Tel: No---------------- Signature-----------**

ج.
**يجوزللموظفإنهاء هذاالعقدلأيسببمنالأسبابمنخلالتقديمإشعارخطيم سبققبل 30 يومًاإلىصاحبالعمل.**

.18. **التجديد**: يجوزتجديدهذاالعقدعنطريقالاتفاقالمتبادل
19. **التعديلوالتغيير**: أيتعديلأو تغيير، وماشابهفيهذاالعقدفي غيرمصلحة العاملدونموافقةوزارةالعملوالشؤونالاجتماعيةلنيكونلهاأيتأثير على هذا العقد.
20. **تسويةالمنازعات**: يتمتسويةجميعمطالبات وشكاوىالموظف المتعلقةبعقدالعملوفقاًللقانون ولقواعدوأنظمةوسياساتالشركات. فيحالةالتسوية،يتمتسويةالمسألةبطريقةوديةبمشاركةالبعثةالإثيوبية المناسبة
(سفارةأوبعثةدائمةأومكتبقنصليةعامةأوقنصليةفخريةعامة). فيحالةفشلالتسويةالودية،تقدمالمسألةإلىالجهةالحكوميةالمختصةأوال .مناسبة في (البلدالمضيف) أوفيإثيوبياحسبخيار الطرفالمشتكي

.21
**يجبعلىالموظفمراعاةقواعدشركةصاحبالعملوالالتزامبالقوانينذاتال صلةفيالبلدالمضيف**

.22
**صاحبالعملمسؤولعنالحصولعلىتأشيرةالدخولاللازمةوتصريحعملق .انونيللموظفمنالبلدالمضيف**

**23. القانونالواجبالتطبيق:**
**تخضعأحكاموشروطالعملالأخرىالتيتتفقمعالاحكام الواردة أعلاهللقوانينذاتالصلة.........................**

**24. إذاتم انتهاكهذاالعقدمن طرف صاحبالعمل،فقدوافقمكتب التوظيفعلىأنيكونمسؤولابالتكافل والتضامن.**

**25. يتمإبرامعقدالتوظيفهذافيأربعنسخ،نسخةلمكتب التوظيفونسخة لصاحبالعملونسخة .للموظفوتودعالنسخةالأخيرةفيوزارةالعملوالشؤونالاجتماعية**

**------- - اليوم-----نحن الموقوعون علىهذاالعقد:**
**الموظفصاحبالعملالخاصوكالةالتوظيف**
**عنوان ----------------------------------------**
**التوقيع ------------------ هاتف: ----------------**
**2.الاسمالكامل ----------------------------------------**
**عنوان ----------------------------------------**
التوقيع ------------------ هاتف: ---------------
**جيم ممثل الوكالة .3**
**الاسم الكامل..........................................**
**عنوان............................................ ...........**
**ص ب :صندوق............................................ ....**
**رقم الهاتف. ............................................ ...**
**فاكس ............................................ ...........**
التوقيع ......................................